«የኢንተር ሚላን ደጋፊ ነኝ»

ስዜና ንባብ ስክረን ላይ ኮትና ከረቫቱን አድርጎ ገጭ ሲል /በነገራችን ላይ ኮትና ከረቫት የሚያደርገው ስዜና ብሎ ብቻ አይደለም/ ከዜናው ይልቅ እሱ ከብዶ ይታያል። መደበኛ ህይወቱ ግን በቴሌቪዥን እንደሚታየው «ሲሪየስ» አይደለም። ይልቁንም ነገሮችን አቅልሎ በመመልከት ምክንያት እየፈለገ ይቀልዳል። የዛሬ 35 ዓመት እንኳ ተፈሪ መኮንን ተማሪ በነበረበት ወቅት የስኮላርሺፕ ዕድል አግኝቶ የት/ቤቱ የአካዳሚክ ክፍል ሀላፊ የሆኑት ካናዳዊ የድጋፍ ደብዳቤ ሲፅፉለት በትምህርቱ ላይ ስላለው ትጋትና ስለውጤታማነቱ ከገለፁ በኋላ «He has a sense of humor» ብለውት ነበር። ከውጪ ቋንቋዎች እንግሊዝኛ፣ ጣሊያንኛና ፈረንሳይኛን አቀላጥፎ የሚናገረው ፍፁም ጌታቸው በራሱ የሚተማመን፣ ለስራው ቅድሚያ የሚሰጥ፣ በሰው ጉዳይ ጣልቃ የማይገባ፣ ህይወትን ቀለል አድርጎ መመልከት የሚወድ ነው። ፍፁም 20 ዓመታት ያህል ስለኖረባት ስለጣሊያን፣ ስለሙያውና ስለግል ህይወቱ ሲያወጋን የዚህ እትም እንግዳ ሆኗል።

ቀም ነገር፡- ከልጓ ጎደሎምሳሌ እድ ስልማት ከተቀበሉ ተማሪዎች አንዱ ነበርክ ሲባል ሰምታለሁ፤ ምን ትዝ ይልሃል?

ፍፁም፡- በየጎመራ ክፍት/ቤቱ በከፍተኛ ማዕረግ ያለፉ ተማሪዎች ቤተመንግስት ግብዣ ተደርጎ እዚ ጎይለሥላሴ ሽልማት ያሰጡ ነበር። የዚያን ሰለት መጀም ልዩ ቀን ነው። ከወላጆቼ ጋር ነበር የሄድኩት። መጀመሪያ ሁሉም ተማሪዎች 12ኛ ክፍል መጨረሳቸውን የሚያረጋግጥ ዲፕሎማ ከሳቸው እጅ ይቀበላሉ። ከዚያ ደግሞ በየከፍሉ በከፍተኛ ማዕረግ ያለፉ ተማሪዎች እየተጠሩ ሽልማት ይቀበላሉ። ጃንሆይን በሙሉ ዓይን ማየት አይቻልም ይባል ስለነበር እየፈራሁ ነበር ስጠራ የሄድኩት። አጠገባቸው ስደርስ ዙፋኑ ላይ ቁጭ ብለዋል። ስእጠገባቸው የተሰያዩ ሰዎች አሉ። ልክ ሽልማቴን ሲሰጡኝ ጨበጠው «እንዚአብሔር ይባርክህ» ይላሉ።

ቀም ነገር፡- ምንድነው የተሰጠዎከው?

ፍፁም፡- ሁለት ወርቅ ቅብ ብዕርና ሃስትና የታሪክ ያልብ ወለድ መፅሀፍትን ነው የሸለሙኝ።

ቀም ነገር፡- ሽልማቶቹ ስቡን ስሱ?

ፍፁም፡- አንደኛው ብዕር አሰ። አንደኛው ግን አባቴ የት አንዳደረገው አላውቅም። መፅሐፍቶቹ ግን አሁንም አሉ። የሚገርምህ ብዕሩ ላይ «ጎይለሥላሴ ዘ ፈርስት» የሚል ፅሑፍ አለው።

ቀም ነገር፡- የዚያን ጊዜ ስንት ዓመትህ ነበር?

ፍፁም፡- 12ኛ ክፍል ስጨርስ 16 ዓመቴ ነው። ት/ቤት የገባሁት በ4 ዓመቴ ነው።

ቀም ነገር፡- የት ነው የተወለድከው?

ፍፁም፡- የተወለድኩት አዲስ አበባ አትራቢያ ደብረዘይት ነው። ከመምህራን ቤተሰብ ነው የተወለድኩት። እናቴም አባቴም መምህራን ነበሩ።

ቀም ነገር፡- ትምህርትስ?

ፍፁም፡- የእንደኛ ደረጃ ትምህርቴን እስከ 6ኛ ክፍል በእዚ ልብነድንግል ነው በሃን መርዕድ ገብቼ እስከ 8ኛ ድረስ ተማርኩ። ከዘጠነኛ እስከ 12ኛ ደግሞ ተፈሪ መኮንን ተምሬ ጨረስኩ።

ቀም ነገር፡- ውጤት ስጣም ጥሩ ነበር። የደረጃ ተማሪ ስለነበርክ ስማዕረግ ነው ያሰፍኑት። በ1962 ዓ.ም ጨርሼ በቀዳማዊ ጎይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በ1963 ዓ.ም ገባሁ።

ቀም ነገር፡- ምን ነበር የምታጠናው?

ፍፁም፡- እንደ ገባን የምንማረውን የትምህርት ዓይነት አንመርጥም ነበር። ለአንድ ዓመት ያህል ከተማርን በኋላ ባገኘነው ውጤት መሠረት ነበር የምንደለገውን ዲፓርትመንት የምንመርጠው። ውጤቴ ጥሩ ስለነበር አንደኛ የሞላሁት ህግ ነበር። አባቴ እንኳን ወደህክምናው ገብቼ ዶክተር እንድሆን ነበር የሚፈልገው። እኔ ግን እያደኩ ስመጣ የታሪኻ ዶክተር መሆን አይደለም። የታሪክ ሰው መሆን ወይም ሥነ-ፅሑፍ ማጥናት ነው የታሪኻ። አንደኛ ህግ፣ ሁለተኛ ታሪክ፣ ሦስተኛ ቋንቋ ሞላሁ። ጥሩ ውጤት ስለነበረኝ ህግ ዲፓርትመንት ስሜ ወጣ።

ቀም ነገር፡- እንዴት ህግ መረጥክ?

ፍፁም፡- የሚገርምህ ወደህግ ዲፓርትመንት ስንገባ ተመሳሳይ ጥያቄ ተርቦልን ነበር። የዚያን ጊዜ የዲፓርትመንቱ ሀላፊው የውጪ ዜጋ ሲሆን ዲን ፖል ይባል ነበር። ትምህርት ከመጀመራችን በፊት አየተጠራን ኢንተርቪው ነበረን። ጠቅላላ 35 ልጆች ነበርን። ለኢንተርቪው ስገባ ቢሮ ውስጥ ብቻውን ነበር። «Why you want to be a lawyer?» አለኝ። የምጠብቀው ጥያቄ ስለነበር አልተደናገጥኩም። ድሮ አያቴ የፍ/ቤት ክርክር በተደጋጋሚ ስለነበራቸው «ዛሬ ተጠር አሰኝ ያዛሬ ሳምንት ተጠር አለኝ» እያሉ ሲሄዱ አስታውሳለሁ። ይህንን ታሪክ አስታውሼ በዚህ የተነሳ የአያቴ ጉዳይ ነው ወደህግ እንዳዘነብል ያደረገኝ አልኩት። በጣም ደስ አለው። መነሻ ይፈልጋል ወደአንድ ዲፓርትመንት ለመግባት።

ቀም ነገር፡- ትምህርቱን ሳትጨርስ ታዲያ እንዴት ወደመጪ እገር ሄደክ?

ፍፁም፡- ትምህርት ጀምረን አንድ ዓመት ያህል እንደተማርን በቀጣዩ ዓመት ማለትም 1964 ዓ.ም አጋማሽ ላይ የተማሪዎች ንቅናቄ ወጣ። ረዳሻ ስለነበር ት/ቤት ተዘጋ። ከዚያ ያው ዩወቅቱ እየተሰዳደብን ስለማን፣ ስለቼጉቬራ፣ ስለማርክስ መወያየት ተጀመረ። በመሀል የጣሊያን መንግስት በትምህርት ሚኒስቴር ዘርፉ የስኮላርሺፕ ዕድል ለሰባት ልጆች ይሰጣል። ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ አይቼ አመለከትኩ። ትምህርቶቹ በህግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በኢንጂነሪንግና በህክምና ናቸው። የተሻለ ውጤት የነበረንን ተማሪዎች መለመሉትና ስኢንተርቪው 4 ኪሉ ትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ጠሩን። አንድ ሰባት 'ይሆናሉ ኢንተርቪው የሚያደርጉት ሰዎች «ለምንድነው ጣሊያን ሄደህ ለመማር የፈለከው?» የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ። ፈረንሳይኛ ስለማውቅ በጣሊያንኛ መማር እንደምፈልግ ነገርኋቸው።